**ለኢትዮጵያ የሚድያ አውታሮች በሙሉ**

**ከግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ጽ/ቤት**

**የሰኔ 1 1997 ዓ.ም የዴሞክራሲ ስማእታትን በሚመለከት የተላለፈ መልእክት**

ሰኔ 1 2002 ዓ.ም

ዛሬ ሰኔ 1 ቀን ነው:: የዛሬ 5 አመት በእዚህ እለት በምርጫ የሰጠነው ድምጻችን ይከበር በማለት በሰላማዊ መንገድ ጥያቄ ለማቅርብ በወጡ የሃገሬው ዜጎቻ ላይ የመለስ ዜናዊ አምባገነናዊ አገዛዝ በወሰደው አረመኒያዊ የእመቃ እርምጃ ከ40 በላይ የሚሆኑት ህይወታቸው አልፏል። በሽህ የሚቆጠሩ ዜጎችም አሰቃቂ ቅጥቀጣና የወህኒ እንገራ ተፈጽሞባቸዋል።

ይህን እለት እነዚህን የዴሞክራሲ ሰማእታት አስበን የምንውልበት ነው። እለቱን እያስታወሱም በሃዘን ለሚሰቃዩ የቅርብ ቤተሰቦቻው፣ ዘመዶቻቸውና እውቆቻቸው እኛም ሰማእታቱን ያልረሳናቸው መሆኑን የምንገልጽበት እለት ነው።

እለቱ ሰማእታቱ የወደቁለትን የዴሞክራሲ ሰንደቅ ከፍ አድርገን በማውለብለብ ዛሬ በሃገራችን ላይ የሰፈነውን አምባገነናዊ አገዛዝ፣ ህዝብ በነጻነቱ በመረጠው መንግስታዊ አስተዳደር እንዲተካ በማድረግ ሰማእታቱን ለዘላለሙ ህያው ለማድረግ ቃል የምንገባበትነው። የወደቁት ህዝብ በነጻ የምርጫ ድምጹ የሚሾመውና የሚሽረው ፈሪሃ ህዝብ የሚሰማው መንግስት በኢትዮጵያችን ለማየት ነውና።

በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በሙሉ እነዚህን ሰኔ 1 ቀን 1997 ኣ. ም በግፍ የተጨፈጨፉ ወገኖቻችንን አብረውን እንዲያስታውሷቸውና የወደቁለትንና የሁላችንም የሆነውን በሃገር ዴሞክራሲ የማስፈን ምኞታቸውን ከግብ ለማድረስ በጋራ እንድንነሳ ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ወገናዊ ጥሪውን ያቀርባል።

ዘላለማዊነት ለስማእታቱ!!!

ክስመት ለአምባገነንነት!!!

ከግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ጽ/ቤት